Ee-JRIF
Ethiopian e-journal
For Research and Innovation Foresight

# የአድዋ ድል "*በዕድል*"?

## ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ዕውቀት መለዋወጫ መረብ፥

*የትግሬ ነፍጠኛ፣ የሸዋ ፈረሰኛ፣ የጎጃም እግረኛ፣ የአማራ ስልተኛ ከብ ይቀላው፣ ያናፋው፣ ያንደገድገው ጀመር።*
*ከእንዝርት  የቀለለ የጁየ፣ ከነብር የፈጠነ ቤጌምድሬ፣ ከቋንጣ የደረቀ ትግሬ፣ ከአሞራ የረበበ ሸዌ፣ ከንብ የባሰ ጎጃሜ*
*እያባረረ በየጎዳናው ዘለሰው። አውሬ የነጩው ነጭ መንጋ እየመሰለ በየዱር ሆዱን ገልብጦ ወደቀና የአሞራ ቀለብ ሆነ።*

**መጋቢት ፲፰ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ. ም.**

በወለላዬና በዶክተር ተድላ ሀሳብ ላይ ተጨማሪ፥

በቅድሚያ ክብር በደምና በአጥንታቸው አንድነት ሀገር ላቆዩልን ለአድዋው ጀግኖች በሙሉ፥ ወለላዬ በስዊድን የመቶ ሃያ አንደኛው ዓመት የአድዋን ድል መዘክርና በዝግጅቱ ላይ የነበሩትን ክስተቶች ስላሳወቁን ብቻ ሳይሆን ምላሽ በመስጠትዎና ለሚመለከተውም ጥሪ በማድረግዎ ምስጋናችን የላቀ ነው። በእኛም በኩል የመቶ ሃያ አንደኛው ዓመት የአድዋን ድል በመጣጥፎች ለመዘከር ዝግጅት በምናደረግበት ጊዜ አንዳንዶቻችን የእቴጌ ጣይቱን ታላቅ አስተዋጽዖ ለብቻው ማዘጋጀት ጀምረን፥ ነጥለን የምናወጣው ታሪክ ጎደሎ ሆኖ ስላገኘነው አድዋን ከመላው ጀግኖቹ ጋር መተረኩ የተሟላ ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህ ጽሑፍም በስዊድን የመቶ ሃያ አንደኛው ዓመት የአድዋን ድል ለመዘከር እ. ኤ. አ. ማርች አምስት (፭) ቀን (፪) ሁለት ሺህ  አስራ ሰባት (፲፯) ዓ. ም. በነበረው ዝግጅት ላይ ፕሮፌሰር ተከስተ ነጋሽ ያደረጉት ንግግር፣ ስንትና ስንት ሕይወት የተከፈለበትን የአድዋን ድል በዕድል ነው የተገኘው ማለታቸው ከአንድ አፍሪካዊ የሚጠበቅ ነው? ለምንስ  ንግግራቸው ከቀድሞው የደቡብ አፍሪካ መሪ ከሚስተር ታቦ ምቤኪና ከፕሮፌሰር ዮናስ ሬይሞንድ ተቃራኒ ሆነ? ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬንና ታቦ ምቤኪን በማገናኘት የሰጡት የግል አስተያየትስ የጓደኛቸው የፕሮፌሰር ማሞን ጥልቅ የምርምር ጽሁፎችና አፍሪካዊ ስራዎች ያንጸባረቀ ትክክለኛ መረጃ ነው? መረጃቸውና ንግግራቸውስ አነጋጋሪ ሆኖ "*ሶስቱንም አጣጣሉ*" ተብለውስ ለምን ስማቸው እንዲነሳ አደረገ?  የምኒልክን ባህርይ የሚጻረር በመናገራቸውም '*እምዬ ምኒልክ ወላዋይ ነበሩ ወይ?*'[2] ብለው ወለላዬ የተባሉ ጸሐፊ በኢትዮሚድያ ድህረ ገጽ ላይ እንዲጠይቁ ስላነሳሳቸው ይህን ጥያቄ የታሪክ ባለሙያዎች በአግባቡ እንደሚመልሱት በመተማመን በዚህ ጽሑፍ ለጊዜው ከታላቁ የአፍሪካውያን ድል አንጻር ለመዳሰስ እንሞክራለን።

በቅድሚያ እቴጌ ጣይቱንና ታሪካዊ ድርሻቸውን ካለዳግማዊ ምኒልክ ታሪክና ስብህና ማግዘፍ ይቻላል? በታሪክስ አይደለም በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ዛሬ በሰለጠነው ዓለም የትኛው ወንድ፣ የሀገር መሪ፣ ወይም ባለስልጣን ነው የትዳር አጋሩን፣ ሴትን ጦር ሜዳ ድረስ ይዞ የሚሄድ? አይደለም ትናንት ዛሬስ የትኛው ወንድ ነው ከውጭ ሀገር ሰዎች ጋር በሚደረግ ወሳኝ የሀገር ጉዳይ ስብሰባ ላይ ሚስቱ እንድትገባና በውይይቱም የሴት ሀሳብ እንዲሰማ የሚፈቅድ? ዳግማዊ ምኒልክ ግን ጥንት በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ሴትን በሴትነቷ አክብረው፣ ጦር ሜዳ ላይ ሴት ልጅ ምን መስራት እንደምትችል ለዓለም ያስመሰከሩ፣ አድዋ ላይ ሴትንና ሀገራቸው ኢትዮጵያን ክብር ያጎናጸፉ ፈር ቀዳጅ አፍሪካዊ መሪ ነበሩ።

በእርግጥ በዓለም ላይ በስልጣኔ ያደገና የዘመነ ምዕራባዊ ሀገር፣ በስልጣኔዋ ዝቅተኛነት በናቋት፣ በአንዲት አፍሪካዊት ሀገር መሸነፍን መቀበል ቀላል አይደለምም። አይጠበቅምም። በተለይም በሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሰባት (፲፰፻፸፯) ዓ.ም. ጀርመን፣ በርሊን[3] ላይ ሃያላኑ የአውሮጳ ሀገራት አፍሪካን ለመቀራመት ያቀዱትን ዕቅድ ደጋግመው እንዲያጤኑት ያደረገውን፣ ዓለምን ያስደመመውን፣ ምዕራባውያን ሳይወዱ በግዳቸውም ቢሆን የሚቀበሉትን ታላቁ የአፍሪካውያንን ድል (የአድዋን ድል) መቀበል ለምዕራባውያን እጅግ በጣም ከባድ ነው። ይልቁንስ ምላሹ በጊዜው የኢትዮጵያ መሪ የነበሩትን ዳግማዊ ምኒልክን ስማቸውንና ስራቸውን ማጉደፍ ብቻ ሳይሆን በድሉ ባለቤት፣ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የተወሰደው የበቀል እርምጃ ዛሬም መቆሙ አጠያያቂ ነው። በተቃራኒው ግን አፍሪካውያንን ለነጻነታቸው ያነቃቃው ታላቁ የአድዋ ድል በዓለም ላይ ላሉ ለነጻነት ናፋቂዎች በሙሉ የነጻነት አርማ ነው። በመሆኑም ከአድዋ ድል በኋላ ጣሊያንና የቅኝ ግዛት ህልማቸው የተጨናገፈባቸው ምዕራባውያን ኢትዮጵያንና መሪዋን የተበቀሉበትና የሚበቀሉበት መንገድ፣ ከአርባ ዓመታት በኋላ ጣሊያን በድጋሚ ኢትዮጵያን በመውረር የተከለከለ የመርዝ ጭስ በመጠቀም ከሰላሳ ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ቀን እስከ መፍጀት ያደረሳቸው የበቀል እርምጃ ለአፍሪካዊያን በሙሉ ግልጽ በመሆኑ ለፕሮፌሰር ተከስተም አይጠፋቸውምና ኢትዮጵያ ያሸነፈችው በዕድል ነው መረጃውም ያለው በተሸናፊው፥ በወራሪው፥ በጣሊያን እጅ ነው ማለት የፕሮፌሰር ተከስተን የቀድሞ ስራዎች ለተከታተለ ሰው እውን ይህ አባባል የእርሳቸውን

---

1 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 208-210)

2 http://www.ethiomedia.com/1000codes/was-emperor-menelik-wishy-washy.pdf

3 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 337-338)

የምርምር ስራ ይመጥናልን ያሰኛል።

በተለይ ከምንም በላይ ***<u>ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ዕውቀት መለዋወጫ መረብ፥</u>*** በእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃሉ ***<u>Ee-JRIF: (V. 9, No. 1)</u>*** ***<u>Ethiopian electronics Journal for Research and Innovation Foresight)</u>*** ***በዘጠነኛው እትም፥ ቁጥር አንድ፥ ልዩ እትሙ፥ የመቶ ሃያ አንደኛው ዓመት የአድዋን የድል በዓልን*** ለመዘከር የካቲት ሃያ ሶስት (፳፫) ቀን ሁለት (፪) ሺህ ዘጠኘ (፱) ዓ.ም. **(March 2nd, 2017)** በታተመው ልዩ እትሙ፥ ከጦርነቱ በፊትና በኋላ ምዕራባውያን ጋዜጦች[4] ምን እያሉ ስለአድዋ ጦርነት ይጽፉ እንደነበር፥ በመረጃ ተደግፎ የተዘረዘረው፥ በዶክተር ተድላ ተክሌ የቀረበው ሰፊ የምርምር ጽሁፍና ሌሎችም ከጦርነቱ ጋር የተያያዙ መጣጥፎች በድህረ ገጹ ላይ ከወጡ በኋላ በመሆኑ የፕሮፌሰር ተከስተን ንግግር ምሁራዊ ትንታኔ  አጠያያቂ ያደርገዋልና የወለላዬን ብዕር አይንጠፍ እያልን '*እምዬ ምኒልክ ወላዋይ ነበሩ ወይ?*' የሚለው ጥያቄን ለመመለስ ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ጸሐፊዎች የጻፉትን ለጊዜው ብናቆየው ጥንት በዚያ ዘመን ምኒልክ የወሰኑዋቸውን ውሳኔዎች፥ በጊዜው ከወሰዱዋቸው እርምጃዎቻቸው ጋር በማነጻጸር የንጉሱን ወላዋይ መሆን አለመሆን እስቲ እንፈትሽ።

ዳግማዊ ምኒልክ ለአድዋ ጦርነት ለመዘጋጀት ሲያስቡ ለአምስት ዓመታት ያህል ታላቅ ረሀብ በኢትዮጵያ በመከሰቱ ከባድ የረሀብ ዘመን ነበርና በረሀቡ ምክንያት የሚሞተው ቀባሪ ያጣበት፣ የጋማ ከብት ስጋ የተበላበት፣ ሰራዊቱ የተመናመነበት፣ በባህላዊና ጊዜው ባለፈበት የጦር መሳሪያ በመጠቀም ጣሊያንን ለመከላከል አቅም የመነመነበትና መኳንንቱም ተከፋፍለው በነበረበት ሰዓት በመሆኑ ለጣሊያን ቅኝ ግዛትን ለማስፋፋት የተመቸ ጊዜ ነበርና ይህንን ሁሉ ለማስተካከል ንጉሰ ነገስቱ ጊዜ ስላስፈለጋቸው የመጀመሪያዎቹን የንግስና ዓመታት ምኒልክ ጥሩ ግኑኝነት ለመፍጠርና ሃይል ለማጠናከር በመጠቀም በሶስትና አራት የንግስና ዓመታት ውስጥ፥

- ከጣሊያን ጋር ያለውን ግኑኝነት ያለሳልሱ ጀመር።
- መኳንንቱም ተደልለው ስለነበር በዘዴ በመያዝ አዲስ አበባ ጋብዘው በፍቅርና በደስታ ተቀብለው ታማኝነታቸውን አረጋገጡላቸውና መኳንንቶች ሁሉ ከምኒልክ ጎን ቆሙ።
- የውስጥ ችግሮቻቸውን እያቃለሉ አታለዋቸው የነበሩትን ጣሊያኖችም እያታለሉ በዚህ ሁሉ መሀል መሳሪያ ማደራጀታቸውን ቀጠሉ።
- ከሶስትና ከአራት የንግስና ዓመታት በኋላ ያልተከፋፈለና የተነቃቃ ሕዝብ፣ በመሳሪያ የተደራጀ፣ ለመሪው ለምኒልክ ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ ሰራዊት፣ ጠንካራ ክንድ ያለው ብርቱ መሪ ለመሆን በቁ።

***ደካማና ወላዋይ መሪ ይህንን ሁሉ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል ወይስ አርቆ ሀሳቢና ብልህ መሪ?***

- ከአድዋው ጦርነት በፊት ለምኒልክ የውጫሌው ዉል አለመስተካከል ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም የአውሮጳ መንግስታት የጣሊያንን የቅኝ ግዛት ዓላማ በድምጽ ብልጫ በማጽደቃቸው አዝነው ስለነበር በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ጣሊያኖች በሙሉ "*<u>ከሀገሬ ይውጡልኝ ወደፊትም አይምጡብኝ</u>*" ብለው ዶ/ር ትራቬርሲ በተባሉት ለጣሊያን መንግስት ደብዳቤ ሲልኩ የጣሊያን መንግስት ግን ምኒልክን ለመደለል ሁለት ሚሊዮን የጥይት ስጦታ ቢልክላቸው ምኒልክ ግን "*<u>እናንተ ጠብ ፈለጋችሁኝ እንጂ እኔ ወዳጅነታችንን  ነው የምፈልገው</u>*" በማለት ስጦታውን ተቀብለው ጣሊያኖችን በሙሉ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ ያደረጉ በስጦታው ያልተደለሉ[5] *በሀገራቸው ሉዓላዊነት የማይደራደሩ በመሆናቸው ነው ወይስ ወላዋይ?*
- አድዋ ላይ የጦሩ አዛዥ ባራቲዬሪ የያዘው ምሽግ ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ሰራዊትን በግላጭ ለማጥቃት ስለሚመቸው በሌላ በኩል ደግሞ ዘማቹ ከቤቱ ከወጣ ከሰባት ወራት በላይ በማለፉ የሰራዊቱ ስንቅ፣ የከብቱም ቀለብ እያለቀ በመሆኑ ምኒልክ ከበው ለመቀመጥ ከሰባ ሺህ በላይ የሚጠጋው ሰራዊታቸውን የሚቀልብ ስንቅ ስለሌላቸው ሰራዊታቸውን ላለማስጨረስ ጦርነቱ ቶሎ እንዲካሄድ ፈልገው፥ ባራቲዬሪ በሰላዮቹ የኢትዮጵያውያንን እንቅስቃሴ ለማወቅ ሲሞክር የውስጥ አርበኞች የኢትዮጵያን ጦር አሳንሰው በመንገር፥ መኳንንቶቹም እንደታመሙ በማስመሰል፥ ስንቅ እንዳለቀና ንጉሱም ወደኋላ ለመመለስ አስበዋል መባሉን ባራቲዬሪ እንዲሰማ በማድረግ፥ (*ፕሮፌሰር ተከስተ የጠቀሱት መረጃ ይህ የታለሉበትን ነው?*) የውስጥ አርበኞች እነባራቲዬሪ ከምሽጋቸው ወጥተው እንዲዋጉ አነሳስተው ጣሊያኖችን አታለዋቸዋል። ምኒልክም በውስጥ አርበኞቻቸው በኩል የባራቲዬሪ ህቅድ በምስጢር ስለሚደርሳቸው፥ ባራቲዬሪ ለውጊያ ሲወስን የጠላትን ዝግጅት አስቀድመው ማወቅ ስለቻሉ ለመዘጋጀትም ጠቀማቸው። ጦርነቱም በፈለጉት መንገድ እንዲመራ ክፍተታቸውንም ለማስተካከል ጠቅሟቸው አቋማቸውን ደብቀው በሙሉ ልብ ጦርነቱን እንዲመሩ

---

4 http://www.nesglobal.org/eejrif4/index.php?journal=admin&page=issue&op=current

5 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928 ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ 1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 113)

አስችሏቸዋል። ሰራዊቶቻቸውን ላለማስጨረስ ጦርነቱ ቶሎ እንዲጀመርና በፈለጉበት መንገድ እንዲሄድ ማድረግ *አስተዋይ ብልህና አርቆ ሀሳቢ መሪ ችሎታ ነው ወይስ የደካማና የወላዋይ?*

- በአድዋው ጦርነት አራት ሺህ ያህል የጣሊያን ምርኮኞች[6] በተማረኩበት ጊዜ ምኒልክ በአዋጅ ምርኮኞችን ሰው እንዲቀልብ በየመኳንንቱ ቤት ምርኮኞችን የሰጡ፣ ለምርኮኞችም ለመንገዳቸው ምግብና መድሃኒት የቆሰሉትም ወደ አዲስ አበባ የሚጓዙበት በቅሎ እንዲሰጣቸው፣ አዲስ አበባ ሲደርሱ ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ በማድረጋቸው ምኒልክ *የተናቀው የኢትዮጵያ መንግስት የሰለጠነ መሆኑን ነው ያስመሰከሩት ወይስ ያልሰለጠነ ደካማና ኋላ ቀር?*
- ከጦርነቱ በኋላ ብዙ ሺህ የጣሊያን ምርኮኞችን ለማስለቀቅ የጣሊያን የመጀመሪያው ሙከራ ምኒልክን እንታረቅ በማለት በማታለል ምርኮኞች ከተለቀቁ በኋላ ኢትዮጵያን በአዲስ መልክ ሊዋጋ ማሰቡን ምኒልክ በመጠርጠራቸው "***<u>አዲስ ውል ተዋውለን የውጫሌ ውል መፍረሱን ለዓለም ነገስታት ሁሉ ካላሳወቃችሁ ምርኮኞችን አልለቅም</u>***"[7] በማለታቸው ጣሊያን ምርኮኞችን አስለቅቆ ውጊያ የመግጠም እቅዱ ስላልተሳከለት ጳጳሱ ሊዎን አስራ ሶስተኛ ለምኒልክ ምርኮኞችን እንዲለቁ ደብዳቤ ጻፉላቸው። ምኒልክ ግን  ጳጳሱን በጣሊያን በኩል ያለውን እንዲያስተካክሉ ጠይቀው ምርኮኞቹን እንደማይለቁ ያሳወቁት *ጽኑህ መሪ በመሆናቸው ነው ወይስ ወላዋይ?*
- በመጨረሻም ጣሊያን ምርኮኞቹን ለማስለቀቅ ምኒልክ የጠየቁትን በሙሉ ለመፈጸም ሁኔታዎች ስላስገደዷት የውጫሌውን ውል የሚሰርዝ አዲስ ውልና ለጦርነቱም የሚከፈል ካሳ ተካቶበት ምርኮኞቹ እንዲለቀቁ ቢስማሙም ምኒልክ ግን በአንድ በኩል የአውሮጳ መንግስታት ማወቃቸውን ለማረጋገጥና የሚሉትንም መስማት ስለፈለጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጣሊያን መንግስት ማህተም ያለበት እዲስ የውል ሰነድ እስኪደርሳቸው ድረስ ምርኮኞቹን ከአምስት ወራት በላይ አቆይተው የጠየቁት ሲሟላላቸው ብቻ ምርኮኞቹን የለቀቁ ለነጮች ያልተበገሩት *አስተዋይና ብልህ በመሆናቸው ነው ወይስ ደካማና ወላዋይ?*

***<u>የሸዋ ገዢ ሳሉ፥ ከአድዋው ጦርነት በፊት ምኒልክንና ስራቸውን የሚገልጹትን ሁኔታዎች ደግሞ ብንመረምር፥</u>***

- በአጤ ቴዎድሮስ ስርወ መንግስት እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋትና እስረኞቻቸውን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ባሰቡ ጊዜ ልክ እንደ አጤ ዮሐንስ ምኒልክንም ከጎናቸው እንዲሰለፉ ጠይቀዋቸው ነበር። ምኒልክ ግን የእንግሊዞችንና የአጤ ዮሐንስን ወዳጅነት ስለሚያውቁ፥ አጤ ቴዎድሮስ እንግሊዝን ካሸነፉም እንዳይወጉዋቸው በማሰብ መልስ ሳይሰጡ ቆይተው እንግሊዞች በድጋሚ ሲጠይቁዋቸው "*<u>የምትመጡት ኢትዮጵያን አስገብሮ ለመያዝ ከሆነ በነገራቹ አልስማማም</u>*"[8] የሚል ጽኑ መልስ *በሀገራቸው ሉዓላዊነት የማይደራደሩ አርቆ ሀሳቢ በመሆናቸው ነው ወይስ ደካማና ወላዋይ?*
- ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በኋላም እንግሊዞቹ ለትግሬው ገዥ ለደጃዝማች ካሳ ላደረጉት ውለታ የጦር መሳሪያ ሰጥቷቸው ስለነበር ደጃዝማች ካሳ የጎጃሙን ንጉስ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው በ(፲፰፻፷፬) ዓ.ም.  በመላው ኢትዮጵያ ከነገሱ በኋላ የማረኩትና በስጦታ ያገኙትን መሳሪያዎች ተጠቅመው ሸዋን ለማስገበር ጦርነት ሲያውጁ የሸዋው ገዢ ምኒልክ ግን አቅማቸውን በማመዛዘን ለአጤ ዮሐንስ እየገበሩ የራሳቸውን ግዛት በማጠናከር ሃይላቸውን ማደራጀት የቀጠሉት[9] *አቅማቸውን ማመዛዘናቸው ወላዋይ በመሆናቸው ነው ወይስ አስተዋይና አርቆ ሀሳቢ?*
- በአጤ ዮሐንስ ስርወ መንግስት ምኒልክ የጎጃሙ ራስ አዳልን ጦር ለመግጠም ደብረ ታቦር ከገቡ በኋላ ከራስ አዳል የሚበልጥ የጦር ሰራዊት ቢይዙም ዓባይ ዳር ቆላና ደጋ ዳሞትን ራስ አዳልና ሰራዊቶቻቸው ይበልጥ ስለሚያውቁት ለምኒልክ ሰራዊት ግን አመች ባለመሆኑ ነገሩን በማመዛዘን ወደ ሸዋ መመለሳቸው[10] *ብልህነት ነው ወይስ ወላዋይነት?*
- አጤ ዮሐንስ የምኒልክ ግዛት የነበረውን የከፋን ግዛት ለጎጃሙ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት አሳልፈው እንደሰጡባቸው እያወቁ በ(፲፰፻፸፫) ዓ.ም. አጤ ዮሐንስ የጎጃሙን ራስ አዳልን ሲሾሙ ለምኒልክ ግብዣ ሲደረግላቸው የንጉስ ነገስቱን ጥሪ ተቀብለው መሄዳቸው ታዛዥነታቸውን ለማሳየትና ተባብረው ጉዳት እንዳያደርሱባቸው ጭምር ነው።[11] *ይህስ ጥንቃቄያቸው ብልህነት ነው ወላዋይነት?*

---

6 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 225-226)

7 ጳውሎስ ፥ (ገጽ 222-223)

8 ጳውሎስ ፥ (ገጽ 47)

9 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928 ዓ.ም.  የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ 1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 113)

10 ብላቴን  ፥ (ገጽ 107)

11 ጳውሎስ  ፥ (ገጽ 65)

- በአጤ ዮሐንስ ስርወ መንግስት የእስልምና ሃይማኖት እንዳይኖርና እምቢ ያለውም በሙሉ በሞት ይቀጣ ነበርና በሺህ ስምንት መቶ ሰባ (፲፰፻፸) ዓ.ም. "*<u>በኢትዮጵያ ያለው እስላም ሁሉ በክርስትና እንዲጠመቅ በየአውራጃው ትሕዛዝ ስለአስተላለፉ በዚሁ ዓመት ቢያለበት ያለው እስላም ሁሉ በጭቃ ሹምና በመልከኛ ወደየአቅራቢያው ቤተክርስቲያን እየተነዳ በግድ እንዲቆርብ ተደረገ።</u>*"[12] በተቃራኒው ምኒልክ ግን ሰው በራሱ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖት መቀየርን ያስቆሙ፣ ሰራዊታቸውም እንደአጤ ዮሐንስ ሰራዊቶች እንዳይዘርፍ በአዋጅ በመከልከል ባላገሩን ከጎናቸው እንዲቆም ያደረጉና ሕዝቡ በአጤ ዮሐንስ የተማረረባቸውን ነገሮች በሙሉ ያስወገዱት *አስተዋይና አርቆ ሀሳቢ መሪ በመሆናቸው ነው ወይስ ደካማና ወላዋይ?*
- ልክ እንደ አጤ ዮሐንስ ምኒልክም አጠቃላይ ኢትዮጵያን መግዛት ስለነበረ ሀሳባቸው በአስራ ስምንት መቶ ሰባ ዓ.ም. በ(፲፰፻፸) አጤ ዮሐንስ የወሎውን ኢማም መሐመድ ዓሊን (በኋላ ሚካኤል የተባሉትን) ክርስትና ሲያነሱ ምኒልክ ደግሞ አባ ዋጠውን (በኋላ ኃይለ ማርያም የተባሉትን) ክርስትና አንስተው የወሎ ገዥ ቢያደርጉዋቸውም በአስራ ስመንት መቶ ስልሳ ስምንት ዓ.ም. በ(፲፰፻፷፰) አባ ዋጠው በከዷቸው ጊዜ ተዋግተው ድል ካደረጉ በኋላ ወሎን በሙሉ ዮሐንስ ክርስትና ላነሱት ለመሐመድ ዓሊ ሰጥተው[13]፣ በሕዝብ ፊት ከመሐመድ ዓሊ ጋር ሲበሉ በመታየት (በጊዜው ከእስላም ጋር መብላት እንደ ኃጢሃት ይቆጠር ስለነበር) የወሎ ሕዝብ ምኒልክን ተቀብሎ ገበረላቸው። ለመሐመድ ዓሊም ክርስቲያን የሆነችውን የእንጀራ ልጃቸውን ወይዘሮ ማናለብሽን በማጋባት የሃይማኖት ልዩነት ያልበገራቸው ይህስ *የሀገር መሪነት ችሎታቸውን ያረጋገጡበት ነው ወይስ ደካማና ወላዋይ መሆናቸው?*

ከአድዋ ድል በኋላ ልክ በዓመቱ በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ በ(፲፰፻፹፱) ዓ.ም. የአፍሪካ የነጻነት ተጋድሎ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ምኒልክ አድዋ ላይ በተቀናጁት አፍሪካዊ ድል በሌሉበት ***<u>የአፍሪካና የመላው ዓለም የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ የክብር መሪ</u>*** [14]ብለው የሰየሙዋቸው የጉባኤው መሪዎች ተሳስተው ነው? ድሉስ በዕድል ተገኝቶ ነው የመላው አፍሪካውያንና የዓለም ጥቁሮች ድል የሆነው? ሄይቲስ ምኒልክን አስፈቅዳ የመቶኛ ዓመት የነጻነት በዓልዋን ለምን ኢትዮጵያ ውስጥ አከበረች? በአፍሪካውያን ዘንድ የምኒልክ ስምና አድዋስ ለምን እስከዛሬ ድረስ ታላቅ ተጽህኖ ፈጣሪ ሆነው ቀጠሉ? ለዚህ ይሆን ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች ስራዎቻቸው የተገነዘቡትን ስሜት በማንጸባርቅ አምና ለመቶ ሃያኛው የአድዋ ድል መዘከር አድዋን ዓለም አቀፍ[15] የአፍሪካውያን የነጻነት ተጋድሎ ማህከል እናድርገው የሚል መሪ ሀሳብ ያቀረቡት? በዘንድሮው የአድዋ ድል በዓል (እ.ኤ.አ. ማርች አምስት ቀን ሁለት ሺህ አስራ ሰባት ዓ.ም.) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተገኙት የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ መሪ ሚስተር ታቦ ምቤኪ[16] ለአድዋ ድል ***የአመራር ብቃት፣ ጠንካራ ግኑኝነትና የሕዝብ አንድነት*** ወሳኝ ድርሻ ነበራቸው ብለው እንደ አንድ አፍሪካዊ መሪ የሰጡት ምስክርነትስ የሚያረጋግጠው የምኒልክን ጠንካራ መሪነት ነው ወይስ ደካማነት? ጣሊያኖች በተቀነባበረ የመረጃ ልውውጥ ተታለው የውስጥ አርበኞች የኢትዮጵያን ጦር አሳንሰው በመንገር፥ መኳንንቶቹም እንደታመሙ በማስመሰል፥ ስንቅ እንዳለቀና ንጉሱም ወደኋላ ለመመለስ አስበዋል መባሉን የጦሩ አዛዥ ባራቲዬሪ እንዲሰማ በማድረግ፥ የውስጥ አርበኞች ጣሊያኖችን አነሳስተው፣ ከምሽጋቸው እንዲወጡና እንዲዋጉ ያደርጉዋቸውን የተታለሉበትን መረጃ ነው ጣሊያኖች አለን የሚሉን መረጃ?

ለማጠቃለል ያህል '*<u>እምዬ ምኒልክ ወላዋይ ነበሩ ወይ</u>*?' የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከላይ የዘረዘርናቸው ግኝቶች የሚያረጋግጡት ዳግማዊ ምኒልክ ከጠበቅነው በላይ ከዘመናቸው ቀድመው የተገኙ ብልህ፣ አስተዋይና አርቆ ሀሳቢ መሪ፣ በባህርያቸውም የዋህና ርህሩኅ እንደነበሩ ግልጽ ነውና የተቀረውን ፍርዱን ለአንባቢዎች እየተወን ጸሐፊና የስነ ጥበብ ስራ ባለሙያ የሆኑት ቃልኪዳን ኃይሉ የተባሉት ጸሐፊ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚተላለፉት የጥበብ ስራዎች ላይ ከሰሞኑ በዘሐበሻ ድህረ ገጽ ላይ ባስነበቡን አስተያየት እናጠቃልላለን።

> የኛዎቹ ፊልሞች ደግሞ **ያሸነፍነው አድዋን በገዛ ድራማችን በገዛ ቴሌቪዥናችን ሽንፈትን ያከናንቡናል፤** ጠብቀንና አክበረን ያቆየነውን ***ሥነምግባር*** **በገዛ *ፊልምና* ድራማዎቻችን አፈር እናስበላዋለን፡፡** የሁለት ሺህ አመት የክርስትና ታሪክ ያለን እኛ፤ ከሳውዲ ቀድመን እስልምናን በክብር የተቀበልን እኛ ሃይማኖት የለሽ ሆነን **በገዛ ቴሌቪዥናችን ትናንት እንደተፈጠረ ሕዝብ ታሪክ እንደ አዲስ ሲጻፍ ማየት ያመናል፡፡**[17] (ቃልኪዳን ኃይሉ)

<editor@nesglobal.org>
Ee-JRIF & NES-Global Managing Editors
http://www.nesglobal.org/eejrif4/index.php?journal=admin&page=index

---

[12] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928 ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ 1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 201)

[13] ብላቴን ፥ (ገጽ 105-107)

[14] Pan-African Conference 1897

[15] ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ (February, 2016) (Turning Adwa into a Pan-African Struggle Heritage Global Site! NES Commentary) http://ecadforum.com/2016/02/29/turning-adwa-into-a-pan-african-struggle-heritage-global-site/

[16] አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ መሪ የታቦ ምቤኪ ንግግር ስለአድዋ ድል (Former South Africa President, Thabo Mbeki Speech, In Commemoration of the 121st Anniversary of the battle of Adwa: AAU, Ethiopia (March 4,, 2017) Thabo Mbeki Foundation.

[17] http://www.zehabesha.com/amharic/?p=74151